Maahanmuuttovirasto
Migrationsverket
Finnish Immigration Service

TURVAPAIKKA-, MAAHANMUUTTO- JA KOTOUTTAMISRAHASTO
Euroopan unionin tuella

# በቪዲዮ አገናኝ የጥገኝነት ቃለ መጠየቅ

በቪዲዮ አገናኝ ለሚከናወነው የፊንላንድ የስደተኞች አገልግሎት የጥገኝነት ቃለ መጠይቅ ተጋብዘዋል። በቃለ መጠይቁ ወቅት ስለ መብቶችዎ እና ግዴታዎችዎ አስመልክቶ እነዚህን መመሪያዎች በጥንቃቄ ያንብቡ። ስለእነዚህ መመሪያዎች ማናቸውም ጥያቄዎች ካሉዎት፣ በቃለ መጠይቁ መጀመሪያ ላይ የፊንላንድ የስደተኞች አገልግሎት ሰራተኛ መጠየቅ ይችላሉ።

## የቃለ መጠይቁ አላማ ምንድን ነው?

- በፊንላንድ ለጥገኝነት አመልክተዋል። በፊንላንድ ጥገኝነት የጠየቁበትና ወደ ትውልድ ሀገርዎ መመለስ የማይችሉበትን ምክንያት በቃለ መጠይቁ ላይ ይብራራል።
- በዚህ ቃለ መጠይቅ ሁሉንም የማመልከቻዎትን መሰፈርቶች ማብራራቱ ጠቃሚ ነው። ከቃለ መጠይቁ በኋላ አዲስ መሰፈርቶች ካሉዎት ወይም ከቀድሞዎቹ መስፈርቶችዎ ጋር በተገናኘ አዲስ መረጃ መስጠት ከፈለጉ፣ እባክዎ ስለ ጉዳዩ ወዲያውኑ ለፊንላንድ የስደተኞች አገልግሎት ወይም ይግባኝዎን ላመለከቱበት ፍርድ ቤት ያሳውቁ።
- በቃለ መጠይቁ ወቅት የጥገኝነት ማመልከቻዎ ብቻ ይብራራል። በፊንላንድ ውስጥ የቤተሰብ አባላት ካሉዎት፣ በቤተሰብ ትስስር ላይ በመመስረት የመኖሪያ ፈቃድ ለማግኘት ማመልከት ይችላሉ። ለመኖሪያ ፈቃድ የተለየ ክፍያ የሚያስክፍል ማመልከቻ ማስገባት አለበት።

## በቃለ መጠይቁ ወቅት ያሉዎት መብቶች

- ወደ ቃለ መጠይቅዎ ከሕግ አማካሪ ጋር የመቅረብ መብት አልዎት። የሕግ አማካሪው በራሱ ፈቃድ በቃለ መጠይቁ ላይ ይሳተፋል።
- አማካሪውን እራስዎ ማግኘት አለብዎት። አማካሪውን ወደ ቃለ መጠይቁ ካላመጡ፣ ቃለ-መጠይቁ ያለ አማካሪ ሊቀጥል ይችላል።
- በቃለ መጠይቁ ላይ አስተርጓሚ ይሳተፋል። አስተርጓሚው በቃለ መጠይቁ ወቅት የተነገረውን ሁሉ በአግባቡ መተርጎም ሃላፊነት አለበት። አስተርጓሚው በቃለ መጠይቁ ክፍል ውስጥ በመገኘት ወይም በስልክ ወይም በቪዲዮ አገናኝ ይተረጉማል።
- ቃለ መጠይቅ አድራጊው፣ አስተርጓሚው፣ ተወካዩ እና የህግ አማካሪው ሚስጥር መጠበቅ አለባቸው፣ ይህም ማለት በቃለ መጠይቁ ወቅት የሚሰሙትን ማንኛውንም ነገር ለውጭ ሰዎች ይፋ እንዲያደርጉ አይፈቀድላቸውም ማለት ነው።
- ይሁንና፣ በቃለ መጠይቁ ወቅት የሚነግሩን ጉዳዮች በቤተሰብዎ አባል ማመልከቻ ሂደት ላይ ተጽዕኖ ሊኖራቸው ይችላል። በእነዚህ ሁኔታዎች፣ በቤተሰብዎ አባል ጉዳይ ላይ እነዚህን ጉዳዮች ታሳቢ እናደርጋለን። ይሁን እንጂ፣ መረጃውን ለእነሱ መስጠት እርስዎን ወይም የሚወዱትን ሰው ስጋት ላይ የሚጥል ወይም እርስዎ ላይ ተፅዕኖ የሚያደርግ ከሆነ የቤተሰብዎን መረጃ በሚስጥር ይያዛል። ስለዚህ ጉዳይ ምን እንደሚያስቡ በቃለ መጠይቁ ጊዜ ሊነግሩን ይችላሉ።
- እንደ ደንብ፣ እርስዎን የሚመለከቱ ሁሉም ሰነዶች ምስጢራዊ ናቸው።

## በቃለ መጠይቁ ወቅት የእርስዎ ግዴታዎች

- የጥገኝነት ጥያቄዎ ምክንያቶችን አስመልክቶ የመወያየት እና መረጃ የመስጠት ግዴታ አለብዎት። በቃለ መጠይቁ ጉዳይዎ ላይ ተፅዕኖ ስለሚያደርጉ ሁሉም ነገሮች እውነት መናገርዎ ለእርስዎ የተሻለ ነገር ነው።
- አስቸጋሪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ መወያየትም ለእርስዎ የተሻለ ነው። ለማመልከቻዎ ወሳኝ ሊሆን ይችላሉ።
- ማስታወስ ካልቻሉ ወይም ካላወቁ፣ መልስ ለመፍጠር አይሞክሩ። የሀሰት መረጃ መስጠት የእርስዎን ታሪክ ታአማኒነት ይቀንሳል።
- መጠይቁ ወቅት ትክክለኛውን የግል መረጃዎን ያቅርቡ። ማንነትዎን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ሰነዶች ከሌሉዎት፣ እነዚህን ሰነዶች ለማግኘት የተቻለዎትን ሁሉ ጥረት ማድረግና ለፊንላንድ የስደተኞች አገልግሎት መስጠት ይኖርብዎታል። የእነዚህ ሰነዶች ምሳሌ የሚሆኑት ማንነትን የሚገልፁ ሰነዶች ወይም የጉዞ ሰነድ ናቸው። ይሁንና፣ የፊንላንድ የስደተኞች አገልግሎት ሰነዶቹን ለማግኘት ደህንነትዎን ወይም የሚወዷቸውን ሰዎች ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ማንኛውንም ነገር እንዲያደርጉ ሊጫንዎ አይችልም። ያቀረቡትን የግል መረጃ ወደፊት ለመለወጥ በባለስልጣኑ የተሰጠ አስተማማኝ ማንነትን የሚገልፅ ሰነድ ያስፈልግዎታል።
- የፊንላንድ የኢሚግሬሽን አገልግሎት የግል መረጃዎን እና የማመልከቻዎን መነሻ በስደት ጉዳዮች ጉዳይ አስተዳደር ስርዓት ውስጥ ያስቀምጣል፣ ይህም ይፋዊ መዝገብ ነው።
- የተሳሳተ የግል መረጃ ለባለስልጣን መስጠት ወይም በባለስልጣን መዝገብ ውስጥ የውሸት መረጃ ማስቀመጥ በህግ የሚያስቀጣ ወንጀል ነው።
- ሀሰተኛ የግል መረጃ ወይም ሌላ መረጃ መስጠት ወይም መረጃን መደበቅ ቀደም ሲል የተሰጠ ፈቃድ እንዲሰረዝ እና ሌሎች ጉዳዮችን ሊያወሳስብዎት እንደሚችል እባክዎ ልብ ይበሉ።

## ለቃለ መጠይቅዎ እንዴት እንደሚዘጋጁ

- ከቃለ መጠይቅዎ በፊት ከባለስልጣናት የተቀበሏቸውን ሁሉንም መመሪያዎችና ብሮሸሮች ያንብቡ። ስለ ዱብሊን ሂደት ብሮሹራችንን ማንበብዎ አስፈላጊ ነው። እነዚህ ብሮሸሮች ከሌሎዎት፣ በፊንላንድ የስደተኞች አገልግሎት ድረገጽ ላይ migri.fi/en/brochures-and-publications፣ ‹‹የጥገኝነት እና የዱብሊን አሰራር›› በሚለው ርዕስ ስር ሊያገኗቸው ይችላሉ።
- አስተርጓሚው ወይም ቃለ መጠይቅ አድራጊው ሴት ወይም ወንድ እንደሆነ ለመጠየቅ አሳማኝ ምክንያት ካለዎት ከቃለ መጠይቁ በፊት ስለዚህ ጉዳይ ለእንግዳ መቀበያ ማዕከሉ ሰራተኛ ይንገሩ። የእንግዳ መቀበያ ማዕከሉ ጥያቄዎን ወደ ፊንላንድ የስደት አገልግሎት ያስተላልፋል። በማቆያ ክፍል ወይም በሌላ ተቋም ውስጥ ከሆኑ፣ እባክዎ ለማቆያ ክፍል ወይም ተቋሙ ውስጥ ላለ ሰራተኛ ስለ ምርጫዎ ያሳውቁ። የፊንላንድ የኢሚግሬሽን አገልግሎት ምክንያቱ አሳማኝ መሆኑን ይገመግማል።
- የአካላዊ ወይም የአዕምሮአዊ ጤንነትዎ በቃለ መጠይቁ ላይ ተጽእኖ ሊያመጣ የሚችል ከሆነ፣ እባክዎ ለእንግዳ ተቀባይ ማዕከል ሰራተኛው ያሳውቁ። በፈቃድዎ መሰረት፣ እንግዳ መቀበያ ማዕከሉ ከቃለ መጠይቁ በፊት ጉዳዩን በሚመለከት የፊንላንድ የስደተኞች አገልግሎትን ሊያነጋግር ይችላል። በማቆያ ክፍል ወይም በሌላ ተቋም ውስጥ ከሆኑ፣ እባክዎ ለማቆያ ክፍል ወይም ተቋሙ ውስጥ ላለ ሰራተኛ ስለ ምርጫዎ ያሳውቁ።
- የሚመገቡትን ምሳ ወይም ገንዘብ ይዘው ይምጡ። ከግቢው ውጭ ምሳ ሊመገቡ ይችላሉ።
- በቀን ውስጥ የሚያስፈልግዎትን ማንኛውንም መድሃኒት ይዘው ይምጡ።
- እባክዎ ከቃለ መጠይቁ በፊት ማናቸውንም ተጨማሪ ሪፖርቶችን ለፊንላንድ የስደተኞች አገልግሎት ያቅርቡ። ቃለ መጠይቅዎ በቅርቡ የሚከናወን ከሆነ፣ ከማመልከቻዎ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሁሉንም ሰነዶች እና ማስረጃዎች ይዘው ይምጡ።
- ወደ ቃለ መጠይቁ ካልተጋበዙ በስተቀር፣ ልጆችን ይዘው አይምጡ። በቃለ መጠይቁ ወቅት ልጅዎን የሚንከባከብልዎ ሰው ከፈለጉ፣ እባክዎ ለእንግዳ መቀበያ ማዕከሉ አስቀድመው ያሳውቁ።
- በሰዓቱ ይድረሱ።

## በቃለ መጠይቅዎ ቀን ምን ማድረግ እንዳለብዎ

- ያለ በቂ ምክንያት የቃለ መጠይቁን ቀን መቀየር አይችሉም። በቃለ መጠይቁ ቀን ከታመሙ፣ ስለ ጉዳዩ አንድ ጊዜ ለእንግዳ መቀበያ ማእከል ይንገሩ። ቃለ መጠይቁ ከተጠናቀቀ ከአንድ ሳምንት በኋላ ከእንግዳ መቀበያ ማዕከሉ ውስጥ ከነርሷ ወይም ከሀኪሙ የተሰጠውን ሪፖርት ለፊንላንድ የስደተኞች አገልግሎት መላክ አለብዎት። ያለ በቂ ምክንያት ከጥገኝነት ቃለ መጠይቁ ከቀሩ፣ ቃለ መጠይቅ ሳይደረግልዎ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል።
- ለቃለ መጠይቁ የተጋበዙ ሰዎችና በፊንላንድ የስደተኞች አገልግሎት አስቀድሞ የተፈቀደላቸው ሌሎች ሰዎች ብቻ በቃለ መጠይቁ ላይ መሳተፍ ይችላሉ።
- ድጋፍ ሰጭ ግለሰብ ለማምጣት የሚፈልጉ ከሆነ፣ እርስዎ ወይም ድጋፍ ሰጪዎ ስለዚህ ጉዳይ ከቃለ መጠይቁ በፊት የፊንላንድ የስደተኞች አገልግሎትን በጽሁፍ መጠየቅ አለባችሁ። ከዚያ ውጪ፣ ቃለ-መጠይቁ አድራጊው በቃለ-መጠይቁ መጀመሪያ ላይ ደጋፊዎ በቃለ መጠይቁ ላይ እንዲገኝ ይፈቀድለት እንደሆነ ይወስናል። የድጋፍ ሰጪዎ ግለሰብ የህግ አማካሪዎ መሆን የለበትም እንዲሁም ጉዳዩን ለመመርመር ተሳትፎ አያደርግም።
- ቃለ መጠይቁ የሚከናወነው በፊንላንድ የስደተኞች አገልግሎት ሰራተኛ ነው።

- ቃለ መጠይቁ የሚመዘገብ ይሆናል። የቃለ መጠይቁ ክፍል የCCTV ካሜራም ሊኖረው ይችላል።
- ቃለ መጠይቁ ቀኑን ሙሉ ሊቆይ ይችላል። አስፈላጊ ከሆነ፣ የምሳ እረፍትና ሌሎች እረፍቶች ይኖራሉ። በፈለጉት ጊዜ እረፍት መጠየቅ ይችላሉ።
- አስፈላጊ ከሆነ፣ ቃለ-መጠይቁ በሌላ ቀን ይቀጥላል። በዚህ ሁኔታ፣ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ለቃለ መጠይቅ አዲስ ግብዣ ይደርስዎታል።

## በቃለ መጠይቁ ወቅት ምን ይሆናል?

- በመጀመሪያ፣ ቃለ-መጠይቅ አድራጊው በቃለ መጠይቁ ወቅት ምን እንደሚሆን ይነግርዎታል እንዲሁም መብቶችዎን እና ግዴታዎችዎን እንደተረዱት ያረጋግጣል። ያልገባዎ ነገር ካለ፣ እባክዎ ይጠይቁ። አስተርጓሚውን የሚናገረውን የማይረዱ ከሆነ፣ እባክዎ ለቃለ-መጠይቅ አድራጊው ያሳውቁ።
- ዝርዝር የግል መረጃዎ ከዚህ ቀደም ያልተሰበሰበ ከሆነ፣ ቃለ-መጠይቅ አድራጊው በመጀመሪያ ይህንን መረጃ ይጠይቃል። ቃለ-መጠይቅ አድራጊው ቤተሰብዎ እነማን እንደሆኑ፣ የት እንደኖሩ እና ወደ ፊንላንድ የገቡበትን መንገድ ይጠይቅዎታል። ቃለ-መጠይቅ አድራጊው በፊንላንድ ማመልከቻ ምርመራ ወይም ላለማስተናገድ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ስለሚችሉ መረጃዎች ይጠይቅዎታል።
- ቀጥሎም የትውልድ ሀገርዎን ለምን መልቀቅ እንዳስፈለገዎት እና ለምን መመለስ እንደማይችሉ ቃለ መጠይቅ ይደረግልዎታል። በእርስዎ ላይ ስለደረሰብዎ ነገር ሁሉ በሀቀኝነት እና በተቻለ መጠን በዝርዝር ይናገሩ።
- ቃለ-መጠይቅ አድራጊው ስለተወያዩባቸው አጋጣሚዎች ተከታታይ ጥያቄዎችን ይጠይቅዎታል። በሀቀኝነት ይመልሱ። ካላወቁ ወይም ማስታወስ ካልቻሉ፣ ለቃለ-መጠይቅ አድራጊው ያሳውቁ።
- በቃለ መጠይቁ ጊዜ፣ በእርስዎ ጉዳይ ውሳኔ ላይ ተፅዕኖ ማድረግ የሚችል መረጃን ለፊንላንድ የስደተኞች አገልግሎት መስጠት ይችላሉ። ለምሳሌ ያህል፣ በፊንላንድ ውስጥ በወንጀል ከተጠረጠሩ ወይም በዚህ ሀገር ውስጥ በወንጀል ከተከሰሱ፣ ይህ ክስተት በፊንላንድ የስደተኞች አገልግሎት ጉዳይዎ ሂደት ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል። አስፈላጊ ከሆነ፣ የፊንላንድ የስደተኞች አገልግሎት በቃለ መጠይቁ ወቅት በጉዳዩ ላይ ያለዎትን አስተያየት እንዲሰጡ እድል ይሰጥዎታል።
- የተወሰኑ ጠቅላላ ጥያቄዎች ከሁሉም ጥገኝነት ጠያቂዎች ይጠየቃሉ። ቃለ-መጠይቅ አድራጊው ከሀገር ስለመባረር እና መግባት ስለመከልከል ምን እንደሚሰማዎ ጥያቄዎችን ይጠይቅዎታል።
- የፊንላንድ የኢሚግሬሽን አገልግሎት  አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ቃለ፡መጠይቅ አድራጊው በቪዲዮ ግንኙነት ከፊል ሆነ ሙሉ ቃለ፡መጠይቅ  ከእርስዎ ጋር በማድረግ ጉዳዮን ይገመግማል። ቃለ፡መጠይቁ አድራጊው ቃለ ምልልሱ በትክክል መመዝገብን፡ ከእርስዎ ጋር ሙሉ በሙሉ ለማረጋገጥ ካልቻለ፣ ተጨማሪ እና እርማቶችን የሚያስገቡበት የጊዜ ገደብ ይሰጥዎታል። ለራስዎ ማቆየት የሚችሉትን የቃለ ምልልሱ የግል ቅጂ በፖስታ ይላክሎታል።

## የፊንላንድ የኢሚግሬሽን አገልግሎት ውሳኔ የሚሰጠው እንዴት ነው?

- በማመልከቻዎ መሰረት፣ በግላዊ ሰብአዊነት ምክንያት የተነሳ ወይም በህገ-ወጥ የሰዎች ዝውውር ሰለባ በመሆንዎ የተነሳ የአለም አቀፍ ጥበቃ ወይም የመኖሪያ ፍቃድ ሊሰጥዎት ይችላል።

- የፊንላንድ የኢሚግሬሽን አገልግሎት በጥገኝነት ቃለ መጠይቅዎ ወቅት ባቀረቡት መረጃ እና በጉዳይዎ ላይ በቀረቡት ሌሎች ማስረጃዎች ላይ ተመርኩዞ ለጉዳይዎ ውሳኔ ይሰጣል። የፊንላንድ የኢሚግሬሽን አገልግሎት ውሳኔውን የሚደግፍ መረጃ ለማግኘት የማህበረሰብ ምንጮችንም ሊጠቀም ይችላል።

- አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ፣ የሰነዶችዎን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የፊንላንድ የስደተኞች አገልግሎት የትውልድ ሀገርዎን ሊያነጋግር ይችላል። ባለስልጣኑ ስለዚህ ጉዳይ አያውቁም እንዲሁም የማረጋገጫ ሂደቱ ለእርስዎ እና ለቤተሰብዎ ስጋት አያስከትልም።

- ቃለ፡መጠይቁ አድራጊው የቃለ ምልልሱን በትክክል መመዝገብ፡ ከእርስዎ ጋር ሙሉ በሙሉ ለማረጋገጥ ካልቻለ፣ ተጨማሪ እና እርማቶችን የሚያስገቡበት የጊዜ ገደብ ይሰጥዎታል።እንዲሁም በማመልከቻዎ ላይ ውሳኔ እስኪያገኙ ድረስ ከተሰጠው የጊዜ ገደብ በኋላም ከማመልከቻዎ ጋር የተያያዙ ተጨማሪ መረጃዎችን መላክ ይችላሉ።ሆኖም ከቀነ፡ገደቡ በኋላ የሚቀርቡ ተጨማሪ መረጃዎች በውሳኔው  ግምት ውስጥ ሊገቡ አይችሉም። እባክዎ ተጨማሪ መረጃዎን በጽሁፍ ያቅርቡ።

- በኋላ ላይ ተጨማሪ መረጃን መስጠት ከፈለጉ፣ እባክዎ በጽሁፍ ያድርጉት። የደዋዮችን ማንነት ማረጋገጥ ስለማንችል ስለጉዳይዎ በስልክ አንወያይም።

- ማመልከቻዎ ውድቅ ከተደረገ፣ ወደ ፊንላንድ እና የሼንገን ስምምነት ተጋሪ ወደሆኑ ሌሎች ሀገራት እንዳይገቡ ሊባረሩ እና ሊከለከሉ ይችላሉ።

- ማመልከቻዎ ውድቅ ከተደረገ ወይም እርስዎ ካቋረጡት፣ በፈቃደኝነት ለመመለስ ለድጋፍ የማመልከት መብት አልዎት። ይህ ድጋፍ በአንዳንድ ሁኔታዎች ላይ ይሰጣል፣ እነዚህም ሁኔታዎች ሲያመለክቱ ፍተሻ ይደረግባቸዋል። ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት፣ የእንግዳ መቀበያ ማእከልዎን ይጠይቁ ወይም በፈቃደኝነት ለመመለስ የእርዳታ አድራሻ መረጃን በፊንላንድ የስደተኞች አገልግሎት ድረገጽ https://migri.fi/en/return ላይ ይመልከቱ።

- ምንም እንኳን የጥገኝነት ማመልከቻዎ ዉሳኔ እየጠበቀ ባይሆንም ማንኛውንም አዲስ የጥገኝነት ምክንያት ለባለሥልጣናት ያሳውቁ። አዳዲስ እውነታዎችን ወይም ምክንያቶችን በአስቸኳይ ካላቀረቡ በኃላ በእነሱ ላይ ተመስርተው አዲስ የጥገኝነት ማመልከቻ ቢያቀርቡ ላይመረመሩ ይችላሉ። ስለ አዲሱ መስፈርቶች ቀደም ብለው ላለመናገር ምክንያት ሊኖርዎት ይገባል። እንደ ምክንያት የሚቀመጠውም እራስዎ ላይ ተጽእኖ ማድረግ ያልቻሉት ነገር መሆን አለበት። የፊንላንድ የኢሚግሬሽን አገልግሎት አዲሱን ማመልከቻዎን ይገመግምው እንደሆነ ይመረምራል።